# የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር




## የነርስ/ሚድዋይፍ ባለሞያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ መመሪያ

ግንቦት፣2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ፣ኢትዮጲያ

# ማ ው ጫ

1. መግቢያ ........ 3
2. አጭር ርዕስ ........ 3
3. የመመሪያው አላማ ........ 4
4. ትርጓሜ ........ 4
5. የተፈጻሚነት ወሰን ........ 4
6. አጠቃላይ መርሆች ........ 5
7. የደንብ ልብስ አይነትና ስታንደርዱ ........ 6
8. የደንብ ልብስ የአለባበስ ስርአት ........ 6
9. ተግባር እና ሀላፊነት ........ 8
   1. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባር እና ሀላፊነት ........ 8
   2. የምግብ መድሀኒት የጤና ክብካቤ አስተዳደር ባለስልጣን ተግባር እና ሀላፍነት ........ 8
   3. የክልል ጤና ቢሮ ተግባር እና ሀላፊነት ........ 8
   4. የሆስፒታሎች ማናጅመንት ተግባር እና ሀላፊነት ........ 8
   5. የሜትረን/የነርስ ዳይሬክተር ተግባር እና ሀላፊነት ........ 9
   6. የዋርድ ሀላፊ ነርስ ተግባር እና ሀላፊነት ........ 9
   7. የእስታፍ ነርስ ተግባር እና ሀላፊነት ........ 9
10. መመሪያ ስለመተላለፍ ........ 10

# የነርስ ባለሙያዎች የደንብ ልብስ/ዩኒፎርም/አለባበስ መመሪያ

## 1. መግቢያ

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከክልልና ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮዎች ጋር በመተባበር በጤና ተቋማት የሚሰጠውን አገልግሎት ለማጠናከርና ለማሻሻል የተለያዩ ሪፎርሞችን እየተገበረ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም ሪፎርሞች መካከል የሆስፒታል ሪፎርም አንዱ ነው፡፡ ይህ ሪፎርም መመሪያ በውስጡ አስራ ሶስት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡

የነርሲንግ አገልግሎትን በበቂ ከህሎት ፣በጥሩ ስነምግባር እና አመለካከት ማሻሻል ዋንኛው እና አንዱ የሪፎርሙ አካል ነው፡፡ የነርሲንግ አገልግሎት ካካተታቸው ዋናዋና ነጥቦች ውስጥ የነርሲንግ ባለሙያዎች አለባበስ ስርዓት መዘርጋት እና የስራ ቦታ ንጽህና መጠበቅ ነው፡፡ምንም እንኳን የሆስፒታል ሪፎርም መመሪያ ላለፉት አራት አመታት እየተተገበረ ቢገኝም የነርሲንግ አገልግሎት ማሻሻያ እስታንዳርዶች ትግበራ በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑን እንደማስረጃ መውሰድ ይቻላል፡፡ እንደአብነት የነርሲንግ ባለሙያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ መውሰድ ይቻላል፡፡ የነርሶች የደንብ ልብስ አለባበበስ ስርዓት ባለሙያዎች ለሙያቸው ያላቸውን ክብር ከማሳየቱም ደህንነታቸውንም ከመጠበቁ ባሻገር ህብረተሰቡ በጤና አገልግሎት ድርጅቶች በሚገለገልብት ወቅት አገልግሎት የሚሰጠውን ባለሙያ ማንነት ለማወቅም ያስችለዋል፡፡ በአሁን ወቅት የነርሶች አለባበስ ወጥ ያልሆነ እና መመሪያ የሌለው ስለሆን አለባበሱን ወጥ እና በህግ የተደገፈ ለማድረግ ይህ መመሪያ በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ይፋ ሆኖዋል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የነርስ/ሚድዋይፍ ነርስ ባለሙያዎች የአለባበስ መመሪያ ቁጥር 003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. የመመሪያው አላማ

የዚህ መመሪያ አላማ በሀገራችን ኢትዮጵያ በነርስነት /በሚድዋይፍነት ተመዝግበው በጤና ተቋማት በስራ ላይ ወይም በትምህርት ላይ የሚገኙ ማናቸውም የነርስ/የሚድዋይፍ ነርስ ባለሙያዎች ለልምምድ ወደ ጤና ተቋማት በሚመጡበት ወቅት የሚለብሱትን የደንብ ልብስ አለባበስ ወጥ ማድረግ ነው፡፡

## 4. ትርጓሜ

**የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመርያ፡-**

1. "ነርስ" ማለት ለሙያዉ ትልቅ ፍቅር ያለዉ በነርስነት ሙያ ህብረተሰቡን ለማገልገል በማስተርስ/በዲግሪ/በዲፕሎማ ወይም በTEVT የተመረቀ/ች ሆኖ አግባብ ባለው የባለሙያዎች ብቃት ማረጋገጫ እና ምዝገባ የተመዘገበ/ች ነርስ ባለሙያ ማለት ነው፡፡
2. "ሙሉ የደንብ ልብስ" ማለት ማንኛውም የነርስ ባለሙያ የሙያ ስራዉን ሲያከናውን የሚለብሰው የአልባሳት አይነት ማለት ነው፡፡
3. "ሙያዊ ያልሆነ ሥነምግባር" ማለት ይህንን የአለባበስ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች የሚቃረን ተግባር ማለት ነው፤
4. "ተገልጋይ" ማለት ለራሱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን የጤና አገልግሎት ለማግኘት ሲል በኮንትራት ወይም በሌላ መልኩ ከጤና ባለሙያ ጋር ግንኙነት የሚፈጥር ታካሚ ወ□ም ደንበኛ ነው፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

አጠቃላይ በሁሉም በኢትዮጵያ የመንግስትም ሆነ የግል የጤና ድርጅቶች የሚሰሩ ነርሶች/ሚድዋይፎች እና ለልምምድ ወደ ማናቸዉም የጤና ተቋማት የሚመጡ ተማሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 6. አጠቃላይ መርሆች

1. ማንኛውም ሴት ነርስ ባለሙያ በዚህ መመሪያ የተፈቀደው ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ ይኖርባታል፡፡ ይህ ሙሉ የደንብ ልብስ ማለት ነጭ ሙሉ ቀሚስ/ሱሪ እና ሸሚዝ/፣ ኬፕ፣ ነጭ የነርሶች ጫማ ነው፡፡
2. ማንኛውም ወንድ የነርስ ባለሙያ በዚህ መመሪያ የተፈቀደው ሙሉ የደንብ ልብስ መልበስ ይኖርበታል፡፡ ይህ ሙሉ የደንብ ልብስ ማለት ነጭ ሙሉ ሱሪ እና ሸሚዝ(scrub suit) ልብስ እና ነጭ የነርሶች ጫማ/Doctors Shoes ነው፡፡
3. በክረምት ወይም በብርድ ወቅት ከዩኒፎርማቸው ላይ ጥቁር ሰማያዊ ሹራብ ከላይ ይደርባሉ፡፡
4. በእርግዝና ምክንያት የደንብ ልብስ መልበስ ያልቻሉ ነርሶች እስከወሊድ ድረስ ነጭ ጋዎን መልበስ ይኖርባቸዋል፡፡
5. የነርስ ባለሙያዎች የደንብ ልብስ የአገልግሎት ዘመንን መሰረት ያደረገ መለያ ይኖረዋል፡፡ ይህ መለያ በቀሚሱ ወይም በሸሚዙ አንገት ዙርያ ላይ በ ቪ ሼፕ በሚሰፋ ባለቀለም እስትራይፕ ይሆናል፡፡ የእስትራይፑ ቀለም እና መጠን እንደሚከተለው ይቀርባል:-

   ሀ. የአገልግሎት ዘመናቸው ከአምስት/5/ አመት በታች የሆኑ ማናቸውም ነርሶች የእስትራይፑ ቀለም ባለ 2 ሳ.ሜ አረንጓዴ ይሆናል፣

   ለ. የአገልግሎት ዘመናቸው ከአምስት እስከ አስር /5-10/ አመት የሆኑ ማናቸውም ነርሶች የእስትራይፑ ቀለም ባለ 2ሳ.ሜ ሰማያዊ ይሆናል፣

   ሐ. የአገልግሎት ዘመናቸው ከአስር አመት /10/ አመት በላይ የሆኑ ማናቸውም ነርሶች የእስትራይፑ ቀለም ባለ 2ሳ.ሜ ወይን ጠጅ ይሆናል፣

   መ. በመማር ላይ የሚገኙ ማናቸውም የነርሲንግ ሙያ ተማሪዎች የእስትራይፕ ቀለሙ ባለ 2ሳ.ሜ ቢጫ ይሆናል፡፡

   ሠ. በሀላፊነት ለይ ያሉ ነርሶች/ሚድዋይፎች፡- የቀሚሱ (የሸሚዙ) ደረት ኪስ ላይ ሀላፊነታቸዉን የሚገልፅ ወርቃማ ወደ ጎን ተለጣፊ ፒን እና ሙያዉን የሚመለከት ክብረ በአል ሲኖር ነርስ ዳይሬክተሮች/ሜትረኖች ጥቁር ቡኒ ካባ ይኖራቸዋል፡፡

## 7. የደንብ ልብስ አይነትና ስታንደርዱ

ወንድ/ሴት ነርስ ነጭ ሸሚዝ አንገቱ ቪ የሆነ እጁ ከክርን በላይ፣ነጭ ሱሪ ወገቡ ማሰሪያ ያለዉ እና ነጭ ዶክተር ጫማ ሲሆን፣
ቀሚስ ለሚለብሱ ሙሉ ልብስ አንገቱ ተመሳሳያ ቪ ሆኖ እጁ ከክርን በላይ የሆነ ቁመቱ ከጉልበት በላይ ያልሆነ እና ሁሉም ሴት ነርሶች ነጭ ኬፕ ያደርጋሉ፡፡

- የልብሱ አይነት ጥራቱ 1ኛ 6000ሺ ቴትረን
- ቆዳ ጫማ/Doctors **Shoes**
- ኬፕ ከነጭ ስስ ቴትረን ጨርቅ የተሰራ
- ሹራብ ጥራቱን የጠበቀ ቶሎ የማይበላሽ
- በሁሉም የደንብ ለብስ የኪሱ ጫፍ ላይ የድርጅቱ ስም በተለጣፊ ጨርቅ መፃፍ አለበት

## 8. የደንብ ልብስ የአለባበስ ስርአት

ማንኛውም የነርስ ባለሙያ

- ይህንን መመሪያ ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ህጎች በሚጥሱ መልኩ ስራውን ማከናወን የለበትም፡፡
- አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ የተሰጠዉን የደንብ ልብስ ለብሶ የሙያ ስራውን ማከናወን አለበት፡፡
- በስራ ላይ ሆኖ በደንብ ልብሱ ላይ ማንኛውም አይነት ልብስ መደረብ አይፈቀድለትም፡፡
- ለተገልጋይ ጤንነትና ፍላጎት ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት አምኖ የደንብ ልብስ በአግባቡ መልበስ፡፡
- በስራ ወቅት ከጋብቻ ቀለበት በሰተቀር ሌሎች ጌጣጌጦች እና ረጃጅም የጆሮ ጌጦች ማድረግ  አይፈቀድም፡፡
- የነርሶች ዩኒፎርም የሙያዉ ክብር የሚገለጽበት ለህብረተሰቡ ወይም አገልግሎት ለሚሰጠዉ አካል ማንነቱን የሚረዳበት ከመሆኑም በላይ ወጥ የሆነ ዩኒፎርም

በተገቢዉ ቦታና ጊዜ በመለበስ የባለሞያዉን እና የተገልጋዩን ደህንነት ማረጋገጥ ዋና አላማዉ ነዉ ።

- የጤና ድርጅቶች በመመሪያዉ የጸደቀዉን አይነት ዩኒፎርም የማቅረብ ግዴታ አለባቸዉ ፤
- በኦፐራሲውን፤ በማዋለጃ በድንገተኛ ክፍል እና ተመሣሣይ ቦታዎች የሚሰሩ ነርሶች በቦታዉ ተገቢዉን አለባበስ የመልበስ ግዴታ እና በኪሱ ጫፍ ላይ የሚሰሩበትን ክፍል በተለጣፊ ጨርቅ መፃፍ አለባቸዉ፣
- ማንኛዉም ነርስ የሚለብሰዉ ዩኒፎርም በአግባቡ የተያዘና ንፁህ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባዋል፣
- ከስራ ሰአት ዉጭ ዩኒፎርም ለብሶ መንቀሳቀስ  አይቻልም፣
- በስራ ሰአት ጆሮ ላይ ማዳመጫ (ኢር ፎን )ማድረግ ሬድዮ፣ቴሌቭዥን ማየት

  የተከለከለ ሲሆን ደንበኛን እና ህሙማንን ሲያነጋግሩ ስልክ ማነጋገርና ማስቲካ ማኘክ የተከለከለ ነዉ፣
- ማንኛዉም የነርሶች ዩኒፎርም የህሙማንን፤የሌሎች ሠራተኞችን ክብር በሚጠብቅ መልኩ መሆን ይገባዋል፡፡  በመሆኑም ገላን በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚያሳይ የጨርቅ አይነት መልበስ አይፈቀድም፣
- ወጥ ዩኒፎርም ለመልበስ ችግር የሚገጥመዉ የነርስ ባለሙያ በተለይም ከአካል ጉዳት ጋር ተያያዥ የሆነ ችግር ሲኖር በነርስ ሀላፊዎችና በሆስፒታል ማኔጅመንት ሊስተናገድ ይችላል ፤
- ማንኛዉም ነርስ የሚሰራበትን ቦታ በተለያየ ምክንያት ሲለቅ የለቀቀዉን የጤና ድርጅት ምልክት ያለበትን ዩኒፎርም ለብሶ በሌላ ተቋም ወይንም ቦታ መታየት የለበትም፤
- ጥፍርን ማሳደግ እና በስራ ወቅት ሰዉ ሰራሽ ጥፍር ማድረግ የተከለከለ ነዉ፣
- ሽቶዎች እና የላብ ማድረቂያዋች በጣም የተጋነኑ እና ህሙማንን የሚረብሹ መሆን የለበትም፤
- የሴቶች ፀጉር በንፅህናና በአግባቡ የተያዘ ሆኖ ረጅም ፀጉር በስራ ወቅት ወደ ላይ በአግባብ መያዝ ይገባዋል፡፡ ወንዶችም በአጭር መቆረጥ ይኖርባቸዋል፤

## 9. ተግባር እና ሀላፊነት

የነርስ ባለሙያዎች የደንብ ልብስ በሀገር አቀፍ ደረጃ፣ በክልል ደረጃ እና በሆስፒታል ደረጃ አለባበሳቸው ወጥ ለማድረግ እና ለመመሪያው ተፈጻሚነት የባለ ድርሻዎች አስተዋጽኦ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

### 1. *የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባር እና ሀላፊነት*

- *መመሪያዎች እና ደንቦች ማውጣት፣ ለክልሎች እንዲሁም ለሆስፒታሎች ማስተዋወቅ፤*
- *የመመሪያዉን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ማገዝ እና መከታተል፤*
- *መመሪያዉ በክልሎች ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ*

### 2. *የምግብ መድሀኒት የጤና ክብካቤ አስተዳደር ባለስልጣን ተግባር እና ሀላፍነት*

- *መመርያዉ ተግባራዊ እንዲሆን ይደግፋል ይከታተላል*
- *ይህንን መመሪያ ተግባራዊ መሆኑን ይቆጣጠራል*
- *መመሪያዉን ተግባራዊ በማያደርጉ ላይ ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ይወስዳል*

### 3. *የክልል ጤና ቢሮ ተግባር እና ሀላፊነት*

- ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመሆን *መመሪያዎች* እና ደንቦች ማውጣት ለሆስፒታሎች ማስተዋወቅ፤
- የ*መመሪያዎች ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ ማገዝ* እና *መከታተል፤*
- *መመሪያ* ከመተላለፍ *ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ቅሬታዎች መፍትሄ መስጠት፤*
- የደንብ ልብስ አለባበስ በክልሉ የሰው ሀይል ልማት ላይ እንደ አንድ *መስፈርት አድርጎ መውሰድ፡፡*

### 4. *የሆስፒታሎች ማናጅመንት ተግባር እና ሀላፊነት*

- የሆስፒታሉ ማኔጅመንት ጥራቱን የጠበቀ ሁለት የደንብ ልብስ በአመት መስጠት ይኖርበታል፤
- በየአመቱ በሆስፒታሉ ዉስጥ ለሚገኙት ነርሶች/ሚድዋይፎች ደንብ ልብስ በጀት መመደብ

- ይህ የደንብ ልብስ በአግባቡ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መስፋቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤
- የተሰጣቸዉን የደንብ ልብስ በአግባቡ መለበሱን በየጊዜዉ ይቆጣጠራል ይከታተላል፤
- ደንበኞች ነርሶችን በቀላሉ መለየት እንዲችሉ በደንብ ልብሱ ለይ የትምህርት ደረጃቸዉን እና ማንነታቸዉን የሚገልፅ መታወቅያ(name tag) ማንጠልጠላቸዉን ማረጋገጥ፤

## 5. የሜትረን/የነርስ ዳይሬክተር ተግባር እና ሀላፊነት

- የወጣው የአለባበስ መመሪያ ማክበር እና ማስከበር ይኖርባቸዋል፡፡
- ማንኛዉም የሆስፒታሉ ነርሶች በስራ ለይ እያሉ የሚመለከታቸዉን የደንብ ልብስ መልበሳቸዉን ማረጋገጥ ፡፡
- ለሆስፒታሉ ነርሶች የደንብ ልብስ መመሪያን ከማስተዋወቅ ጀምሮ በፀደቀዉ የስፌት ዲዛይን መሰረት በአመት ሁለት ልብስ እንደደረሳቸው ማረጋገጥ፡፡
- መመሪያው ለማያከብሩ ነርሶች በመመሪያው መሰረት የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡
- አጠቃላይ ለነርሶች/ሚድዋይፎች ለአመት የሚያስፈልገውን የደንብ ልብስ መጠን፣የእስትራይፑ ቀለም እና  የጨረቁ አይነት ፣ ጥራት ለመሚለከተው ክፍል ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

## 6. የዋርድ ሀላፊ ነርስ ተግባር እና ሀላፊነት

- የወጣው የአለባበስ መመሪያ ማክበር እና ማስከበር ይኖርባቸዋል፡፡
- ማንኛዉም በክፍሉ ውስጥ የሚሰሩ ነርሶችን በስራ ላይ የደንብ ልብስ መልበሳቸዉን ማረጋገጥ፡፡
- ያለበቂ ምክንያት በስራ ላይ ሀላፊ ነርስ የደንብ ልብሱን ሳይለብስ ቢገኝ እና በክፍሉ ውስጥ የማይለብሱ ነርሶች ወደ ሜትረን ባማስተላልፍ በቁጥር ዘጠኝ ላይ የተጠቀሰዉ መመሪያ መተላለፍ ቅጣት በሀላፊ ነርስ ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
- በስራ ክፍሉ ለነርሶች ለአመት የሚያስፈልገውን የደንብ ልብስ መጠን፣ የእስትራይፑ ቀለም ለሜትረን ማሳወቅ፤
- የሁሉም ነርሶች የደንብ ልብስ ንጽኅናውን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

## 7. የእስታፍ ነርስ ተግባር እና ሀላፊነት

- የወጣው የአለባበስ መመሪያ ማክበር እና ማስከበር ይኖርባቸዋል፡፡
- የተሰጠዉን የደንብ ልብስ ወደስራ ከመግባቱ በፊት አሟልቶ መልበስ ግዴታ ነው፡፡

- የደንብ ልብስ እና የግል ንጽህናውን መጠበቅ ግዴታዉ ነዉ፡፡
- በሆስፒታል ውስጥ ተሰፍቶ የተሰጠውን የደንብ ልብስ ማሻሻል ወይም መለወጥ አይኖርበትም፡፡

## 10. መመሪያ ስለመተላለፍ

- ሁሉም በስራ ላይ ያለ ነርስ/አዋላጅ ነርስ የደንብ ልብስ መልበስ ይኖርበታል/ ለማይለብሱ ባለሙያዎች የስቪል ሰርቪሱ በሚፈቅደዉ መመሪያ እና ደንብ የሆስፒታሉ ማኔጅመንት እርምጃ ይወስዳል ፡፡
- ለነርስ የተጠቀሰ መመሪያ ለሚድዋይፍ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**ቀን :-** ________________________

**ፊርማ :-**________________________

**የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር**